
# መዝሙር



# መዝሙር

መዝሙር ማለት ምስጋና ማለት ነው። ልዩ ልዩ ስልትና ቃና ባለው ድምጽ የሚዜም በዜማ ዕቃ የሚቀርብ መንፈሳዊ ማኅሌት ነው። በመዝሙረ ዳዊት እንደተመዘገበው «ለእግዚአብሔር በምስጋና ዘምሩ» የሚል ትዕዛዝ ይገኛል። (መዝ 146፥7) ከዚህ ሌላ ቅዱስ ያዕቆብ «ደስ የሚለው ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር» በማለት ጽፏል። (ያዕ 5፥13) ስለዚህ ለክርስቲያን መዝሙር የዘወትር ተግባሩ ሊሆን ይገባል።

መዝሙር በክርስቲያን አምልኮ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አለው። እስራኤላውያን ከጥንት ጀምሮ በተለይም ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ከፀሎትና መጽሐፍን ከማንበብ ጋር መዝሙርን በመዘመር እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። በክርስትናም ከሰብከቱ፣ ከፀሎቱ፣ ከስግደቱ ... ጋር አብዛኛው የአምልኮታችን ክፍል መዝሙር ነው።

መዝሙር ምስጋና እንደመሆኑ መጠን በግልና በሕብረት ከፀሎት ጋር ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መስዋዕት ነው። (ቈላ 4፥2) በብሉይ ኪዳን እንደሚታወቀው የፍሪዳ ወይም የጊደር፤ የበግና የፍየል መስዋዕት በተለያየ ምክንያት ለእግዚአብሔር ይሰዋ ነበር። ነገር ግን ከዚህ ይልቅ እግዚአብሔር ትሑትና የዋህ በሆነ በተሰበረ ልብ የሚቀርብ የከንፈራችንን ፍሬ እርሱም የምስጋና መስዋዕትን እንድናቀርብለት በቃሉ ነግሮናል። (መዝ 49፥14። ዕብ 13፥15 ። ሆሴዕ 14፥2) ብዙዎች ግን መዝሙርን ጊዜ ማሳለፊያ፣ የፕሮግራም መሸጋገሪያ፣ መዝናኛ አድርገው ይዘምሩታል። ይህም ዘማሪው በመዝሙር ሳይሆን በሌላ ሥራና ሃሳብ መጠለፉንና መዝሙርን ግን በተጨማሪነት የሚሰማው የሚዘመረው መሆኑን ያሳያል። እግዚአብሔር ግን ከመዘመራችን በፊት የእኛ ሰውነት ሕያው ቅዱስም መስዋዕት ሆኖ እንዲቀርብለት ይፈልጋል። (ሮሜ 8፥12) መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ ይለናል እንጂ ቀጥታ ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ አይለንም (ዘፍ 4፥4) የእኛ ሕይወት ግን ከዝማሬው ላይ ሳይሆን ብንዘምር እንዲሁ የከንፈር ድካም ብቻ ስለሆነ እንደ ቃየል መስዋዕት ተቀባይነት አይኖረውም።

እግዚአብሔር ሌሎችን እንስሳት ለአንክሮ ለተዘክሮ ሲፈጥር ሰውና መላእክትን ግን የፈጠረው ክብሩን እንዲወርሱና ስሙን እንዲቀድሱ ነው። ቅዱሳን መላእክት ሱራፌልና ኪሩቤል ሁልጊዜ አዲስ ቅኔና «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» በማለት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በመጮኽ እየዘመሩ እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑት ተዘግቧል። (ኢሳ 6፥1-5 ። ራዕይ 4፥8-11 ። መዝ 102፥20) ሰማያውያን መላእክት እንዳመሰገኑት ሁሉ ምድራዊያን ሰዎችም ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋናን ማቅረብ ይገባናል። «ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑት» ይላል (መዝ 95፥1-2) በእርግጥ ሌሎችም ፍጡራን በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑት ተብለዋል። (መዝ 148፥1-13) ሆኖም ከሰውና ከመላእክት በስተቀር የእግዚአብሔርን ክብር የመውረስ ዕድል ስለሌላቸው ምስጋናቸው ጊዜያዊ ነው። ሰውና መላእክት ግን የተፈጠሩት እግዚአብሔርን በማመስገን እንዲኖሩ ነው። ስለዚህ እኛም እንደ ቅዱስ ዳዊት «በየቀኑ ሁሉ እባርክሃለሁ፤ ስምህንም ለዘላለም ዓለምም አመሰግናለሁ» በማለት ልናመሰግን ምስጋናም የዘወትር ሥራችን ሊሆን ይገባል።

## መዝሙር በመጽሐፍ ቅዱስ

በመጽሐፍ ቅዱስ የመዝሙር ታሪክ ከጥንት ጀምሮ ከእምነት ታሪክ ጋር አብሮ ተተርኳል። ከመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ አንዱ መጽሐፍ መጽሐፈ መዝሙር ነው። ይኸውም መዝሙረ ዳዊት የሚባለው ነው። መዝሙረ ዳዊት የተባለው መጽሐፍ በውስጡ ከያዛቸው 150 ያህል መዝሙሮች ብዙዎች

(82ቱ) በዘማሪነት የሚታወቀው የቅዱስ ዳዊት መዝሙራት ስለሆኑ ነው እንጂ በመጽሐፉ ውስጥ በሌሎች መዘምራን (ቆሬ፣ አሳፍ፣ ኤማንና፣ ሐጌ ዘካርያስ ...) ስም የተጠቀሱ መዝሙሮች ይዟል። በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብዙ የእምነት ሰዎች በየምክንያቱ የዘመቻቸው መዝሙሮች ከታሪኩ ጋር ተመዝግበው ይገኛሉ። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን በየዘመናቱና በየጊዜው የፈጸመውን የመዝሙር ታሪክ እንደሚከተለው እናያለን።

## በብሉይ ኪዳን

### *ሀ) እስራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ የዘመሩት መዝሙር*

እግዚአብሔር በበረታች ክንድ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት በሙሴ አማካይነት እስራኤላውያንን ነጻ ካወጣቸው በኋላ ታላቁን የእግዚአብሔርን ማዳን አዩ። ይኸውም ሕዝቡን እስራኤልን ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ቢብስ ካሻገረ በኋላ የሚያሳድዷቸውን ግብፃውያንን ፈርኦንና ሠራዊቱን ፈረሱንና ፈረሰኞችን እግዚአብሔር በባሕር ውስጥ ጣላቸው። ሕዝቡም እግዚአብሔርን ፈሩ በእግዚአብሔርም ባሪያ በሙሴ አመኑ። (ዘጸ 14፥26-31) በዚያን ጊዜም ባሕሩን ከተሻገሩ በኋላ ሙሴና የእስራኤል ልጆች «በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ» በማለት ረጅም መዝሙር ዘምረዋል። የሙሴና የአሮን እህት ነብዪቱ ማርያም ከሌሎች ሴቶች ጋር በመሆን ይህንኑ መዝሙር በከበሮ እየዘመረች መልሳዋለች። (ዘጸ 15፥1-21)

ሙሴ የሕዝብ መሪ ሆኖ ሳለ ከሕዝብ ጋር እግዚአብሔርን አመሰገነ። ዛሬም ቢሆን ታላላቆችም ታናናሾችም እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑት ይገባቸዋል። (ራዕይ 19፥5) የአገር ሽማግሌ፣ አገረ ገዢ፣ የሕዝብ መሪ መሆን ከመዝሙር ሊለይ አይችልም። ማርያምና ሌሎችም ሴቶች በክብር መዝሙሩን መዘመራቸው ምስጋና በጾታም የማይገደብ መሆኑን ያሳየናል። ሴቶችም ቢሆኑ በሕዝብ ጉባኤ በአደባባይ በከበሮ በሽብሸባ በጭብጨባ በእልልታ እያደመቁ ያለፍርሃት መዘመር ይገባቸዋል። (መዝ 67፥25) እስራኤላውያን የዘመሩት መዝሙር ባሕሩን ከፍሎ ባሻገራቸው ጊዜ ያሳየውን የማዳን ኃይል እያወሳ እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ነው። ዛሬም ቢሆን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል የኃጢአትና የሞት ባሕር ተከፍሎ ዲያቢሎስም ወደ ጥልቅ የእሳት ባሕር የተሻገረበትና እኛ የዳንበት ጊዜ ነው። ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ የችግርን የኑሮን የፈተናን ባሕር እየከፈለ በድል ያሻግረናል። እኛም እግዚአብሔርን ካመለክነው ከፍ ከፍ ካደረግንና ካከበርነው በኋላ ባደረገልን ነገር ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል።

### ለ) እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው የምስክር መዝሙር

ይህች መዝሙር ሙሴ የሚሞትበት ጊዜ ሲቃረብ እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች ላይ ወደፊት ምስክር እንድትሆን የተሰጣት መዝሙር ናት። ከሙሴ በኋላ ሕዝቡን በመሪነት የሚረከበው ኢያሱ ከሙሴ ጋር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አብረው እንዲቆሙ ከተደረገ በኋላ ወደፊት ሕዝቡ ሌሎች አማልክትን ሲከተል ምስክር ትሆን ዘንድ ይህችን መዝሙር እንዲጽፍና ለሕዝቡ እንዲያስተምሩ ተደረገ። (ዘዳ 31፥14-30) ይህች መዝሙር «ሰማያት ሆይ አድምጡ እኔም እናገራለሁ ምድርም የአፌን ቃል ትስማ» ብላ በመጀመር (ዘዳ 30፥19 ፡፡ ዘዳ 32፥1 ፡፡ ኢሳ 1፥2) ሰማይና ምድርን ታስመሰክራለች። ይህች መዝሙር የምስክር መዝሙር ብቻ ሳትሆን የትምህርትና የመታሰቢያ መዝሙርም ናት። ሌሎች አማልክት ሲከተሉ ከዚህች መዝሙር ትምህርት አግኝተው እንዲመለሱና የቀደሙትን እውነተኛ የእምነት አባቶቻቸውንና መሪዎቻቸውን እንዲያስታውሱ እንዲያስቡ ታደርጋቸዋለች።

መዝሙር እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ግጥምና ዜማ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም ለሕዝቡ በከንፈሩ የሚተውለት መልዕክትና ትምህርት መሆኑን ከዚህ እንረዳለን። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን በተለያየ ምክንያት አገር በመቀየር፣ በሞት ... አገልግሎታችንን የምናጠናቅቅ ከሆነ በሕዝቡ የሚቀር

መታሰቢያና ትምህርት እንዲሁም ምስክር የሚሆን መልዕክት ያለው መዝሙር ማስተማር ይገባናል። ሕዝበ ክርስቲያኑም ቢሆን ከጥንት ጀምሮ በተለያዩ አባቶች የተጻፉለትን መልዕክት አዘል መዝሙሮች እያስተዋለ ተምሮ በማጥናት ሊመከርበት ሊገሰጽበትና ሊለወጥበት ይገባል።

### ሐ) በዘመነ መሳፍንት ነቢያት ዲቦራና ባርቅ የዘመሩት መዝሙር (መ. መሳ 5)

መዝሙር በዘመነ መሳፍንትም እግዚአብሔር የሚከበርበትና የሚመሰገንበት መንገድ ነበር። ነቢያት ዲቦራና ባርቅ በዘመነ መሳፍንት ለአራተኛ ጊዜ በእስራኤል መስፍን የነበሩ ናቸው። እንደሚታወቀው በዘመነ መሳፍንት በእስራኤል የነበረው መንግስት መንግስተ እግዚአብሔር ስለነበር እግዚአብሔር ሕዝቡን በቅርብ የሚረዳበት ዘመን ነበር። ሕዝቡም ስለሚደረግላቸው ነገር ያመሰግኑታል። በነቢዩት ዲቦራና ባርቅ ዘመን በአሶር የነገሰው የከንዓን ንጉሥ ኢያቢስ ሃያ ኣመት በላይ እስራኤልን ባስጨነቀ ጊዜ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። ነቢዩት ዲቦራ ባርቅን አስነስታ ከአሥር ሺህ ሰዎች ጋር ወደ ታቦር ተራራ አብራው ወጣች። የኢያቢስ ሠራዊት አለቃ ሲሳራ ከነሠራዊቱ በተንቀሳቀሰ ጊዜ እግዚአብሔር በባርቅ ፊት ወጣ። ሲሳራና ሠራዊቱ ድል ተመቱ። (መ. መሳ 4፥1-24)

ከዚህ በኋላ ዲቦራና ባርቅ ለእግዚአብሔር ክብር እየተቀኙ ዘምረዋል። ይኸው በመጻሕፈ መሳፍንት ምዕራፍ አምስት ላይ የሚገኘው መዝሙር ነው። ሲዘምሩም «እኔስ ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ ለእሥራኤል አምላክ እዘምራለሁ» (መ. መሳ 5፥3) በማለት ሲሆን የደረሰባቸውን መከራ በማስታወስ አሁን ደግሞ ባገኙት ድል እግዚአብሔርን በማመስገን ነው።

ዛሬም ቢሆን በችግርና በጭንቅ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ይገባናል። ጩኸታችንንም በመዝሙር ልንገልጽ እንችላለን። (መዝ 119፥1) እግዚአብሔርም ይሰማናል ይደርስልንማል። ታዲያ በመከራና በጭንቅ ጊዜ የልቅሶ ቅኔ እየተቀኘን ያስታወስነውንንና የለመነውን አምላክና አባት በድል ጊዜ በደስታ ልንዘነጋው አይገባም። በእግዚአብሔር ኃይል ባገኘነው ድል ራሳችንን ማመስገን የለብንም። በተለይም የእግዚአብሔርን ሕዝብ የምናገለግል ሰዎች እግዚአብሔርን በሕዝቡ ውስጥ በድል ስናየው በመቀኘትና በመዘመር ልናመሰግነው ይገባል። መዝሙራችንም ያለፈውንና የአሁኑን፤ መከራውንና ድሉን የሚያስታውስ ሊሆን ይገባዋል። እግዚአብሔር ለድል በድል የተገለጠባቸውን ሰዎችን ስም በመዝሙራችን ውስጥ ማንሳት እንችላለን። ለምሳሌ በዚህ መዝሙር ውስጥ የዲቦራ፣ የባርቅ፣ የዛብሎንና የንፍታሌም ነገድ የሄለር ሚስት ኢያኤል ተጠቅሰዋል። (መ. መሳ 5፥1 ። 5፥18 ። 5፥24) እንዲህም ከሆነ በተለይም በአዲስ ኪዳን በሰይጣና ላይ ለተገኘው ድል እግዚአብሔር መሳሪያ ያደረጋቸውን ቅዱሳን በመዝሙራችን ማንሳት ያስፈልጋል። ደግሞ በግልና በማኅበር በደረሰብን መከራና ጭንቀት እግዚአብሔር ድልን ሲሰጠን በመሳሪያነት የተገለጠባቸውን እያወሱ መዘመር ምስጋናችንን በበለጠ ያከብረዋል ያደምቀዋልም።

### መ) መዝሙር በዘመነ ነገሥት

በእሥራኤላውያን ዘንድ መዝሙር በተደራጀ ሁኔታ በመዘምራንና በዜማ ዕቃዎች በዕለተ ሰንበትና በተለያዩ በዓላት ይዘመር የነበረው በዘመነ ነገሥት እንደሆነ መጻሕፍተ ነገሥትን ስናነብ እንረዳለን። ከመደበኛው የመዝሙር አገልግሎት ውጪም በተለያዩ ምክንያቶች ለእግዚአብሔር ክብር ይዘመር ነበር። አሁን በመጠኑ የምንመለከተው በሚከተሉት አራት ነገሥታት ዘመን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸልንን የመዝሙር ታሪክ ይሆናል።

1. በዳዊት 2. በሰሎሞን 3. በኢዮሳፍጥ 4. በሕዝቅያስ

#### 1) መዝሙር በዳዊት ዘመን

ቅዱስ ዳዊት የሚታወቀው በንጉሥነቱ ብቻ ሳይሆን በዘማሪነቱም ጭምር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው የመዝሙር መጽሐፍ በስሙ ተሰይሟል። ከመዝሙሮቹ ውስጥ በሰማንያ ሁለቱ ላይ የእርሱ ስም ተጠቅቷል። ልበ አምላክ የተበለው ቅዱስ ዳዊት በገና በመደርደር መዝሙር የጀመረው ከንጉሥነቱ በፊት ነው። ወደ ሳኦል ቤተ መንግስት እንዲገባ መሰረታዊ ምክንያት የሆነው የኸው በገና

የመደርደር ችሎታው ነበር። በሳሙኤል እጅ ለንጉሥነት ከተቀባ በኋላ በዳዊት ላይ መንፈስ እግዚአብሔር ሲያድርበት በሳኦል ላይ ግን ክፉ መንፈስ አደረበት። ስለዚህ ክፉ መንፈስ እንዲርቅለት ባሪያዎቹ ባቀረቡለት ሃሳብ መሰረት ሳኦል ዳዊትን አስመጥቶ በገና እንዲደረድርለት አደረገ። ክፉው መንፈስም ከሳኦል እንዲርቅለት አደረገ። ክፉው መንፈስም ከሳኦል ራቀ ዳዊትም በሳኦል ፊት ሞገስን ስላገኘ ጋሻ ጃግሬ ሆነ። (1ኛ ሳሙ 16፥14-23) ነገር ግን ሳኦል እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደሆነ ሲያውቅ ፈራው። ብዙ ጊዜ ሊገድለው ፈለገ። እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ለዳዊት ጠላት ሆኖ ቀረ። እግዚአብሔርም ግን ከሳኦልና ከጠላቶቹ ሁሉ እጅ አዳነው። ይህን በተመለከተ 2ኛ ሳሙ 22፥1-51 ያለውን መዝሙር ዘምሯል።

ዳዊት በእሥራኤል ላይ ከነገሰ በኋላ በኤሊ ዘመን መጨረሻ ላይ የተማረከው የእግዚአብሔር ታቦት ከአሚናዳብ ቤት ተመልሶ እንዲመጣ ባደረገ ጊዜ ከእስራኤል ቤት ጋር በሙሉ ኃይሉ ይዘምር ነበር። ይህንንም ሲገልጽ «ዳዊትና የእስራኤል ቤት ሁሉ በቅኔና በገገና በመሰንቆም በከበሮም በነጋሪትና በጸናጽል በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ይጫወቱ ነበር» ይላል። (2ኛ ሳሙ 6፥5) ከዚያም በአቢዳራም ቤት ሦስት ወር ከተቀመጠ በኋላ ታቦቱ ወደ ዳዊት ከተማ ሲመጣ በብዙ ክብር ነበር። ዳዊትም በሙሉ ኃይሉ በእግዚአብሔር ፊት ይዘፍን ነበር። የእስራኤል ቤትም ሆ! እያሉ ቀንደ መለከት እየነፉ እግዚአብሔርን አክብረዋል። የሳኦል ልጅ ሜልኮል ግን ዳዊትን በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይሉ ሲዘልና ሲዘፍን ባየችው ጊዜ በልብዋ ናቀችው በቃልዋም ተናገረችው። እርሱ ግን «በእግዚአብሔር ፊት እጫወታለሁ» ብሎ ሳያፍር ተናገራት። እርሷም እስከ ሞተች ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም። (2ኛ ሳሙ 6፥16-23)

ቅዱስ ዳዊት በተከለው ድንኳን ውስጥ የሚያገለግሉ ሦስት መዘምራን አደራጅቷል። የአለቆችም ስም ኤማን፣ አሳፍ እና ኤይታም ነበር። ለነዚም ከናንያ የሚባል የመዝሙር (የዜማ) አስተማሪ ነበራቸው። አገልግሎታቸውም በተራ በሰሎሞን ነበር። ዳዊት በአጠቃላይ 288 መዘምራን ነበሩት። ዳዊትም በአደባባይ ሳይውል ከእነርሱ ጋር እየተገኘ ይዘምር ነበር። (1ኛ ዜና 15፥16-24 ። 1ኛ ዜና 25፥1-10)

ዛሬም ቢሆን እንደ ቅዱስ ዳዊት ሁለገብ የሆነ የመዝሙር ሰው መሆን ይገባል። ቅዱስ ዳዊት በገና ይደረድር ነበር፤ እየተቀኘም ይዘምር ነበር። ከዚህም የምንረዳው ከመዝሙር ጋር የዜማ መሳሪያዎችን የመምታት ችሎታ ሊኖረን ያስፈልጋል። በየጊዜውም በመቀኘትና በመዘመር እግዚአብሔርን እንድናመሰግን ለሌሎችም ሰዎች እንድንተርፍ ይገባል። የእግዚአብሔር ቃል «ተቀኙለት ዘመሩለት» ይላል (1ኛ ዜና 16፥9) በዚህም እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ብቻ ይሆን ዘንድ ይገባል። ያም ከሆነ ላመስጋኙ እንደ ሳኦል የክፋት መንፈስ እንዳያድርበት ክፉ መንፈስን ያርቅለታል።

ዳዊት ከንጉሥነቱ በፊት ብቻ ሳይሆን በሹመቱና በንጉሥነቱም እያለ ለእግዚአብሔር ዘምሯል። በግሉ ብቻ ሳይሆን ከመዘምራኑ ጋር በቤቱም ብቻ ሳይሆን በአደባባዩ እግዚአብሔርን በመዝሙር አክብሯል። እኛም በሕጻንነታችን ለእግዚአብሔር የመዘመር ፍቅር የነበረንን ያህል በእድሜ ከፍ ብንልም ሥራ ብንይዝም ትዳር ብንመሰርትም ሹመትና ሥልጣን ብናገኝም የዚህ ሁሉ ባለቤት የሆነውንና ለዚህ ያበቃንን ልዑል አምላክ በግልና በሕዝብ ፊት ልናመሰግነውና በሙሉ ኃይላችን ልናሸበሽብለት ይገባል። በዳር ሆኖ የሚዘምሩትን መናቅ እና መተቸት ግን እንደ ሜልኮል መሆን ነው። እግዚአብሔር የሚንቁትን ይንቃቸዋል የሚስቁትንም ይስቅባቸዋል ደግሞም ይቀጣቸዋል። ስለዚህ በተለይም ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ስሙ የተጻፈበት ጽላት ወጥቶ እግዚአብሔር በሚከብርበት በዓለ ንግሥ ላይ እግዚአብሔርን ከማመስገን ጋር ሳናፍር እምነታችንን ልንመሰክር ያስፈልጋል።

ከዚህም ሌላ የበዓል ቀን ዘማሪዎች ብቻ ልንሆን አይገባም። ያ ከሆነ ለተርዕዮ (ለታይታ) ብቻ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ ቅዱስ ዳዊት እንዳደራጃቸው መዘምራን በሁለት በሦስት ቡድን ከዚያም በላይ ተደራጅተን በሰንበት ትምህርት ቤትና በቤተ ክርስቲያን በየሳምንቱ በየተራ ቋሚ የመዝሙር አገልግሎት ልንሰጥ ያስፈልጋል።

## 2) መዝሙር በሰሎሞን ዘመን

ከዳዊት ጀምሮ በተደራጁ መዘምራን የተጀመረው የመዝሙር አገልግሎት እንደቀጠለ ነው። በሰሎሞን ዘመን በበለጠና በተሻሻለ ሁኔታ ይዘመር ነበር። አሁን በዚህ ርዕስ የምናየው ግን ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሰርቶ በጨረሰ ጊዜ እንዴት እንደተዘመረ ይሆናል።

የቤተ መቅደሱ ሥራ እንደተጨረሰ የእግዚአብሔር ታቦት በካህናት አማካይነት ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንዲገባ ተደረገ። በዚህ ጊዜ በሰሎሞን ሳይከፈሉ ሦስቱንም ቡድን መዘምራን ጥሩ በፍታ ለብሰው በጸናጽል በበገና በመሰንቆ በዜማ ዕቃ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። የሚዘምሩትም «እግዚአብሔር ቸር ነውና ምህረቱም ለዘለዓለም ነውና እግዚአብሔር አመስግኑ» የሚል መዝሙር ነበር። ለድምቀቱም ካህናት መለከት ይነፉ ነበር። የእግዚአብሔርም ክብር በደመና ተገልጦ ቤቱን ሞላው። (2ኛ ዜና 5፥11-14)

ከዚህ በኋላ ሰሎሞን ረዘም ያለ ጸሎት አድርጐ የሚቃጠል መስዋዕት ቀረበና ሕዝቡና ካህናቱ ንጉሡም እግዚአብሔርን በመዝሙር አመሰገኑ። ሌዋውያን የዘመሩትም «ምህረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑት» የሚለውን የዳዊትን መዝሙር ሲሆን የዘመሩትም ንጉሥ ዳዊት እግዚአብሔርን ለማመስገን የሠራውን የእግዚአብሔርን የዜማ ዕቃ በመጠቀም ነበር። (2ኛ ዜና 7፥4-7)

ዛሬም ቢሆን የቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ቤት ሲከበርም ሆነ ማንኛውም በዓል ሲከበር ሁሉም መዘምራን ዩኒፎርም ለብሰው መዘመር ይገባቸዋል እንጂ እንደ ዘወትር አገልግሎት ተራ (ሰሞን) መጠበቅ አያስፈልጋቸውም። ሕዝቡም ከመዘምራኑ ጋር በተለያዩ የዜማ ዕቃዎች እያደመቀ እግዚአብሔርን ማመስገን አለበት።

## 3) መዝሙር በኢዮሳፍጥ ዘመን

በአራተኛው የይሁዳ ንጉሥ በኢዮሳፍጥ ዘመን እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በመዝሙራቸው ተገልጦ ጠላቶቻቸውን እናዳሸነፈላቸው ተመዝግቧል። የሞዓብና የአሞን ልጆች ከእነርሱም ጋር ሞአባውያን ኢዮሳፍጥን ሊወጉ በመጡ ጊዜ ኢዮሳፍጥ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ የእግዚአብሔርን ኃይል በጾምና በጸሎት ጠየቀ። እግዚአብሔርም መንፈሱን በሕዝቅኤል ላይ ገልጾ ሰልፉ የእግዚአብሔር ስለሆነ እነርሱም ዝም ብለው በመቆም የእግዚአብሔርን መድኃኒት እንዲያዩ እንዳይፈሩና እንዳይደነግጡ ተናገራቸውም። ማልደውም በመነሳት ከሕዝቡና ከሠራዊቱ ፊት መዘምራንን በእምነት አቆሙ። መዘምራኑም ጌጠኛ ልብስ ለብሰው ነበር። እነርሱም «ምህረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ» የሚለውን መዝሙር ገና ሲጀምሩ እግዚአብሔር ሊወጉዋቸው በመጡት ላይ ድብቅ ጦርን አመጣባቸው እነርሱም ተመቱ። ከዚህ ድል በኋላ ይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች በፊታቸውም ኢዮሳፍጥ ደስ እያላቸው በበገናና በመሰንቆ በመለከትም ወደ እግዚአብሔር ቤት ገቡ። (2ኛ ዜና 20፥1-30)

ዛሬ ግን ምድራዊ የሆነ የእግዚአብሔር ሰልፍ አናይም። ብዙዎች ሰልፈኞች በሽለላ በፉከራ በዘፈን የሚገልጹት የራሳቸውን ኃይል እንጂ የእግዚአብሔርን ኃይል አይደለም። ክርስቲያኖች ግን ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸልን ከሰይጣንና ከሠራዊቱ ጋር በምናደርገው ሰማያዊ ሰልፍ (ጦርነት) ውስጥ በራሳችን ጥበብና ኃይል ሳይሆን በመዝሙራችን የእግዚአብሔርን ኃይል በመግለጥ ልንዋጋውና ልናሸንፈው እንችላለን። ለድል በኋላም ደስ ብሎን እየዘመርን በቤቱ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባል። መዝሙራችንም ጌጠኛ ልብስ በለበሱ መዘምራን ሊመራ እንደሚገባ ከዚህ ታሪክ እንረዳለን።

## 4) መዝሙር በሕዝቅያስ ዘመን

ሕዝቅኤል በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ካህናቱንና ሌዋውያንን ሰብስቦ የእግዚአብሔር ቤት እንዲታደስ አደረገ። ካህናቱንና ሌዋውያኑን የእግዚአብሔርን ቤት ካነጹትና ከቀደሱት በኋላ

ሕዝቅያስ የተለያየ ዓይነት መስዋዕት እንዲቀርብ አደረገ። ይህ መስዋዕት ሲቀርብ መዝሙር እየተዘመረ ነበር። ሕዝቅያስ ጸናጽልና በገና መሰንቆም አስይዞ መዘምራን አቆመ መስዋእቱም ማረግ በጀመረ ጊዜ በእነዚህ የዜማ መሳሪያዎች ታጅቦ የእግዚአብሔር መዝሙር ተጀመረ። ሕዝቡ እየሰገደ መለከት እየነፋ በመዘመር መስዋዕቱን አቅርበው ሲጨርሱ ንጉሡ ሕዝቅያስና አለቆች በዳዊትና በአሳፍ መዝሙሮች እግዚአብሔር እንዲመሰገን አደረጉ ሁሉም በደስታ አመሰግኑ።

እኛም ዛሬ በስእለታችን፣ በስግደታችን፣ በምጽዋታችን፣ በጾማችን፣ በልግስናችን … የምናቀርበው መስዋዕት ሁሉ እግዚአብሔርን በዝማሬ እያመሰገንን ልናቀርብ ያስፈልጋል። ሰዎች ራሳቸውን ከቀደሱና ካቀረቡ በኋላ የእግዚአብሔር መሆናቸውን የሚገልጹ ለስሙ በመዘመራቸው ነው። ከዚህ ታሪክ እንዳየነው የቤተ መቅደስ መታደስ የሰዎችን መታደስ ያሳያል ከዚያ በፊት ያረከሱት ሰዎች ነበሩና። ይህንንም የገለጡት በመዝሙርና በመስዋዕት ነው። የዘመሩትም ቀድሞ በዳዊት ዘመን በተዘመረባቸው የዜማ መሳሪያዎችና መዝሙሮች ነው። ዛሬም ቢሆን በዳዊት ዘመን የነበረውን ሥርዓተ መዝሙር ልንከተል ይገባል። እንደቀድሞ አባቶች በገና በመደርደር ጸናጽልና መሰንቆ በመምታት መለከት በመንፋት የተዘነጋውን የዳዊትን መዝሙር ልናዳብር ይገባል።

## ሠ) መዝሙር ከባቢሎን ምርኮ መልስ

እስራኤላውያን በባቢሎን ምርኮ በነበሩ ጊዜ በባዕድ ምድር በምርኮ አገር መዝሙራቸውን እንዳልዘመሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። (መዝ 136፥1-5) ከባቢሎን ምርኮ መልስ ግን ሁለት መቶ ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩ። (ዕዝራ 2፥65) በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ትእዛዝና ፈቃድ መሰረት ፈርሶ በነበረው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ምትክ በዚያው ቦታ አዲስ ቤተ መቅደስ ለመስራት አናጢዎች መሠረት ሲጥሉ ካህናቱና ሌዋውያኑ በቀድሞው በንጉሥ ዳዊት ሥርዓት መሰረት ልብስ ለብሰው ጸናጽል ይዘው መለከት እየነፉ እግዚአብሔርን አመሰገኑት። የሚዘምሩትም «ቸር ነውና ለእስራኤልም ምህረቱ ለዘላለም ነውና» የሚለውን በማስተዛዘል ነበር። ሕዝቡም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ደስ ብሏቸው በታላቅ ድምጽ እልል ይሉ ነበር። በአንጻሩም ደግሞ የፊተኛውን ቤት ያዩ ሽማግሌዎች በትዝታ ተወስደው በታላቅ ድምጽ ያለቅሱ ነበር። በዚህም የእልልታውንና የለቅሶውን ጩኸት ለመለየት እስከሚያቸግር ድረስ በታላቅ ፍቅር ይዘመር ነበር። (ዕዝራ 3፥1-13) አንዳንድ ፈተናዎችን አልፎ የቤተ መቅደሱ ሥራ በተጠናቀቀ ጊዜ ደግሞ ቅዳሴ ቤቱን በታላቅ ደስታ አክብረዋል። (ዕዝራ 6፥13-18) ከሌሎች የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ጋር መዘምራንም ከግብርና ከቀረጥ ነጻ ሆነው እንደ ቀድሞው ሥርዓት እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር። (ዕዝራ 24 ፡፡ ነህምያ 11፥22-24)

በሌላ በኩል ደግሞ በነህምያ መሪነት የኢየሩሳሌም ቅጥር ከተሰራ በኋላ ሌዋውያኑና መዘምራኑ ከሰፈሩበት ቦታ ተፈልገው መጥተው የምረቃውን (የቅዳሴውን) በዓል በደስታና በምስጋና በመዝሙር አክብረዋል። አጥሩ ከመሰራቱ በፊት መዘምራኑ በኢየሩሳሌም መንደሮች ሰርተው ነበር። ከዚያም ተሰብስበው ራሳቸውን ካነጹ በኋላ አመስጋኞች በሁለት ተርታ ተከፈሉ። እንደ በጸሀፊው በዕዝራ መሪነት አንዱም በነህምያ መሪነት ቅጥሩን እየዞሩ በእግዚአብሔር ሰው በዳዊት የዜማ ዕቃ በታላቅ ድምጽ ዘምሩ በዚህን ጊዜ የመዘምራን አለቃ ይዝረህያ ይባል ነበር። (ነህምያ 12፤27-43)

ከባቢሎን ምርኮ በኋላ በአጠቃላይ የመዝሙር ሁኔታ እንደቀድሞው ሥርዓት ቀጥሏል። መዝምራኑም የዳዊትንና የሰሎሞንን ትዕዛዝ ጠብቀዋል። ልክ እንደ ዳዊት እንደ አሳፍ ዘመንም የመዘምራን አለቆች ነበሩ። መዘምራኑም በዘሩባቤልና በነህምያ ዘመን እንደሌሎች አገልጋዮች ሁሉ በየዕለቱ የሚገባቸውን ዕድል ፈንታ ከእስራኤላውያን ያገኙ ነበር። (ነህምያ 12፤44-47) በዚያ ዘመን ከነበሩት ነብያት የሐጌና የዘካርያስ መዝሙሮች በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ። (መዝ 145፤146-148)

ከዚህም ታሪክ ብዙ ነገሮችን እንገነዘባለን በባዕድ ቦታ እንደ አሕዛብ የሆኑ ዓለማውያን ሰዎች ሊያሾፉበት ሊዝናኑበት እንድንዘምርላቸው ቢጠይቁን መታዘዝ የለብንም። መዝሙር ምስጋና እንጂ መዝናኛና መታወቂያም መሆን አይደለምና። በቤተ ክርስቲያን ለምናደርገው የመዝሙር አገልግሎት ግን ያለጸታ ገደብ መዘምራን በመሆን መዘመር እንችላለን። ፈርሶ የነበረ የሰው ልጆች ሕይወት፤ ፈርሶ የነበረ ጉባዔ፤ ፈርሶ የነበረ ሥርዓት እንደቀድሞው ሲመለስ ልክ እንደ እስራኤል ወንዱም ሴቱም ልጆችም በአንድ ድምጽ ልንዘምር ይገባል። ስንዘምርም ፍቅራችን የሚገለጸው በደስታ እልል በማለት ብቻ ሳይሆን በታላቅ ልቅሶም ሊሆን ይችላል። ከዚህም አንዳንድ መዝሙሮችን በማስተዛዘል (በመቀባበል) መዝሙሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን እንረዳለን።

በሕዝብ ውስጥ ታላቅ ቦታ የነበራቸው ከመዘምራን ዕዝራ፤ ከባለሥልጣን ነህምያ፤ ከነቢያት ሐጌና ዘካርያስ አብረው ዘምረዋል። ዛሬም እንዲሁ ሊሆን ይገባል። በተለይም በወንጌል ሥራ ውስጥ መዝሙር ትልቅ ቦታ ሊሰጠው ይገባል ልክ እንደ ነህምያ ዘመን በንጽሕና ለሚያገለግሉ መዘምራን ሊታሰብላቸው ሊጸለይላቸው ይገባል። በእግዚአብሔር ፊት በታላቅ አገልግሎት የተሰየሙ ናቸውና።

## 2) በአዲስ ኪዳን

በጌታችን በሐዋርያት ዘመን የጌታ ተከታዮች ይዘምሩ እንደነበር በአዲስ ኪዳን ክፍል ተገልጧል። በብሉይ ኪዳን የተገለጸውም የቤተ መቅደስ የመዝሙር አዘማመር በአዲስ ኪዳን መንፈስ እየተመሰጠረ ሊቀጥል ይችላል። በአዲስ ኪዳን ክፍል የተመዘገበውን ያህል በሚከተሉት አርዕስቶች የመዝሙርን ታሪክ እናያለን።

1) የሆሳዕና መዝሙር
2) የምሴተ ሐሙስ መዝሙር
3) የወህኒ ቤት መዝሙር
4) የማኅበር መዝሙር

### *1ኛ) የሆሳዕና መዝሙር*

ይህ መዝሙር የተዘመረው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወት መጨረሻ አካባቢ ወደ ኢየሩሳሌም በገባበት ጊዜ ነው። መዝሙሩም «ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ሆሳዕና በአርያም» የሚል መዝሙር ነው (ማቴ 21፤9) መዝሙሩን የዘመሩት የጌታ ደቀ መዝሙርት (ተከታዮች) ናቸው። (ሉቃስ 19፤36) በተለይም ሕጻናት በዚህ ቀን በይበልጥ ዘምረዋል። (ማቴ 21፤15) የሚዘምሩትን ጌታ በአህያ ውርንጭላ ሆኖ ወደ ከተማ ሲገባና መቅደሱን ሲዞር ብዙ ሆነው በማጀብ፤ በፊትና በኋላ ሆነው የዘንባባ ዝንጣፍ ይዘው ልብሳቸውን እያነጠፉ በታላቅ ፍቅርና መገዛት ነበር። (ማር 11፤6-10) በዚያን ጊዜ ደስ ብሏቸው በታላቅ ድምጽ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ የቻሉት ተአምራትን ሁሉ ስላዩ ነው። (ሉቃ 19፤37) ፈሪሳውያን ምስጋናውን ቢቃወሙም ጌታ አልተቀበላቸውም።

የእግዚአብሔር ቃል «እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ ለአሕዛብም ሥራውን አውሩ ተቀኙለት ተአምራቱንም ሁሉ ተናገሩ» ይላል። (1ኛ ዜና 16፤8-9) ዛሬም ቢሆን ዓለምን በድንቅ አሰራር የፈጠረውንና በፍቅር ያዳነውን እግዚአብሔርን ስለፍቅሩ ስለማዳኑና ስለ ተአምራቱም ልናመሰግነው ይገባዋል። «ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው» የሚለው መዝሙር አስቀድሞ በቅዱስ ዳዊት በመዝሙር 117፤25 ላይ የተነገረ ነው። ዛሬም የሆሳዕና በዓል ሲከበር መዝሙር 117ን በሙሉ ቄሱ በከፍተኛ ድምጽ ሲናገር ህዝቡ «በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ብሩክ ነው።» እያሉ እየመለሱለት በዚህ ዓይነት እንዲባል የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ያዛል። (አንቀጽ 101) በዚህ በዓል ልክ እንደዚያን ጊዜ ሰዎች ዘንባባ በመያዝ ታሪኩን የሚያስታውሱ ማዳኑን የሚገልጽ መዝሙር በስሙ የተሰየመውን (ካህን፣ ጽላት፣ መስቀል) አጅበን በብዙ ክብር ልንዘምር ይገባናል። (ራዕይ 7፤9-10)

እግዚአብሔር ለወደደው ይገልጣል። ተምረናል የሚሉት የካህናት አለቆችና ጻፎች ፈሪሳውያን እያሉ የሆሳዕናውን መዝሙር የገለጠው ላልተጠበቁ ሰዎች በተለይም ለሕጻናት ነበር። የካህናት አለቆች ጻፎችና ፈሪሳውያንም ማመስገን ሲያቅታቸው «እነዚህን የሚሉትን አትሰማምን? ደቀ መዝሙርትህን ገስጻቸው» በማለት ተመቀኙ። ጌታ ግን «ከሕጻናትና ከሚጠሉት አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ» የሚለውን የዳዊትን ቃል ጠቅሶ «እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮሃሉ» በማለት መልሶላቸዋል። (ማቴ 21፤14-17። ሉቃ 19፤39-40። ዕዝ 8፤2) እንደ ፈሪሳውያን እግዚአብሔር በሕጻናትና በምእመናን እንዳይመሰገን የሚቃወሙ ሰዎች ቢኖሩም እንኳ እርሱ ግን እንደ ድንጋይ ከምንሆነው ከእኛ ምስጋናን ያዘጋጃል። እኛም ማንኛውም ተቃውሞ ሳያግደን እንደ ሕጻናቱ በታላቅ ፍቅር ልንዘምርለት ያስፈልጋል።

### *2ኛ) የጸሎተ ሐሙስ መዝሙር*

ይህ መዝሙር ጌታና ሐዋርያት የዘመሩት መዝሙር ነው። ጌታችን በዚያ ምሽት እግራቸውን አጥቦ ሥጋውንና ደሙን ከሰጣቸው በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ከመውጣታቸው በፊት ዘምረውታል። (ማቴ 26፤30) ያ ምሽት ጌታ ከሐዋርያት ጋር የሚቆይበት የመጨረሻው ምሽት ነበር ለማለት ይቻላል። ሆኖም የመዝሙሩ ቃል ምን እንደሆነ አልተገለጠም። ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ጌታ ለመከራና ለስቅላት የሚያዝበት ምሽት ስለሆነ ለሐዋርያት የሐዘን ምሽት ነበር። ሐዋርያት ከጌታ ጋር ይህን መዝሙር በምን ዓይነት የባባ ልቡና እንደዘመሩት ከዚህ መረዳት ይቻላል። በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሰረት «ዝማሬ» የሚባለው መዝሙር ለዚህ የምሴተ ሐሙስ መዝሙር መታሰቢያ እንዲሆን ከቅዱስ ቁርባን በኋላ ይዘመራል። ከዚህም ሌላ የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ከሕፅበተ እግር ሥርዓት በኋላ ሕዝብ ከቄሱ ጋር መዝሙር 150ን እየዘመረ የዚያን ምሽት ታሪክ ያስታውሳል። (አንቀጽ 122)

ጌታችን ከሐዋርያት ጋር አብሮ መዘመሩ በአዲስ ኪዳን ለሁላችንም አርአያ ለመሆን ነው። ዛሬ በዓለም ላይ ወደ መከራ ሲሄድ እያለቀሰ እንጂ እየዘመረ የሚሄድ ብዙ የለም። ዛሬ በስንብት ጊዜያችው በሰላም እንኳ ቢለያዩ እየዘፈኑ በሥጋዊ ሥርዓት የሚሰነባበቱ ብዙ ሰዎች ናቸው። ክርስቲያን ግን በማንኛውም የስንብትም ሆነ መንፈሳዊ ፍቅርን በሚገልጽ ፕሮግራም ላይ በየምክንያቱ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባዋል።

### *3ኛ) የወኅኒ ቤት መዝሙር*

ይህን መዝሙር የዘመሩት ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ሲላስ ናቸው። የዘመሩትም በወንጌል አገልግሎት ምክንያት በደረሰባቸው መከራ ተደብድበው ከቆሰሉ በኋላ በወኅኒ ተጥለው ከግንድ ጋር ተጠርቀው ሳሉ ነበር። በዚያ የመከራ ሰዓት ቁስላቸው ሳይሰማቸው እግዚአብሔርን በዜማ አመስግነውታል። የሚዘምሩትም ከጸሎት ጋር ነበር። መዝሙራቸው በንባብ ሳይሆን በዜማ ስለነበር በመንፈስም ስለነበር የሌሎችን እስረኞች ልቡና ነበር። እስረኞችም ያደምጡአቸው ነበር። እንዲያውም በመዝሙሩ የተነሳ አንዳንድ ተኣምራት በመታየታቸው ይጠብቃቸው የነበረውን ዘበኛ እንኳን ከነቤተሰቡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አሳምነው ለመዳን አብቅተውታል። ዘበኛውም በእግዚአብሔር ስላመነ ከነቤተሰቦቹ ጋር ሐሴት አድርጓል። ምናልባትም ደስታቸውን የገለጡት በመዝሙር ሊሆን ይችላል። (ሐዋ 16፤25-34)

ከዚህ የምንረዳው መዝሙር በወንጌል አገልግሎት ውስጥ የነበረውን ኃይል ነው። ዛሬም ቢሆን ቃሉን በቀጥታ ብንነግራቸው ለማይገባቸውና ለማይቀበሉን ሰዎች አስቀድመን ስለእነርሱ እየጸለይን ብንዘምር በመዝሙር ልንስባቸው እንችላለን። ከዚህም ሌላ በመዝሙር ውስጥ በማናስደምጣቸው ልናስተምርና ልንሰብክ ይገባናል። ዛሬ ግን ብዙዎቻችን መከራ ሲደርስብን እናማርራለን እንጂ እንኳን በዜማ በግጥምም በቃላትም አናመሰግነውም። ብናመሰግንም ብንዘምርም ከጸሎት ጋር ስላልሆነ የከንፈር ልማድ ብቻ ሆኖ ይቀራል። ነገር ግን መዝሙራችን እስራትን እስከመበጠስ መሰረትን እስከማናወጥ የታመሙትን እስከ መፈወስ ድረስ ኃይል ይኖረዋል። እንዲህ ከሆነ የኑሮና ኃጢአት እስረኞች የሆኑትን ብዙ ሰዎች ተቃዋሚዎቻችንን እንኳ ሳይቀር የጌታ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል።

*4ኛ) የማኅበር መዝሙር*

የማኅበር መዝሙር ስንል በአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች በማኅበር የሚዘምሩትን መዝሙር ነው። ቅዱስ ጳውሎስ «በምትሰበሰቡበት ጊዜ እያንዳንዱ መዝሙር አለው ትምህርት አለው … ሁሉ ለማነጽ ይሆናል» ብሏል። (1ኛ ቆሮ 14፤26) እንደገናም በመዝሙርና በዝማሬ መንፈሳዊም ቅኔ እርስ በእርሳችሁ ተነጋገሩ። ለጌታም በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ» ይላል። (ኤፌ 5፤19። ቈላ 3፤16) እነዚህ ጥቅሶች የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በማኅበር ሲሰበሰቡ ይዘምሩ እንደነበር ያስረዱናል። ከዚህ በፊት የተመለከትናቸው የሆሳእናው መዝሙር፤ የምሴተ ሐሙስ መዝሙር በማኅበር የተዘመሩ ናቸው። ጳውሎስና ሲላስም በእስር ቤት ሳሉ በዜማ እግዚአብሔር ማመስገናቸው በዚያም ዘመን በክርስቲያኖች ዘንድ መዝሙር ምን ያህል ትልቅ ቦታ እንዳለው የሚያስረዳ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ጥቅስ ሆነው የቀረቡ አንዳንድ የጥንት ክርስቲያኖች የኅብረት መዝሙሮች እንዳሉም የሚናገሩ አሉ። ለምሳሌ ኤፌ 5፤14

ከዚህም ሌላ በአዲስ ኪዳን የምናየው በዮሐንስ ራዕይ ስለማኅበር መዝሙር የተገለጸውን ይሆናል። ይኸውም አራቱ እንስሶችና ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች (ኪሩቤልና ሱራፌል) እልፍ አእላፍ መላእክትን በሰማይና በምድር ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ የተለያየ አዲስ ቅኔ እንደዘመሩ የሚገልጽ ነው። (ራእይ 5፤6-14) ይህም በማኅበር ሆነው የዘመሩት ሲሆን የመዝሙሩ ዋነኛ መልእክትም ስለታረደው በግ የሚያወሳ ነው። ሲዘምሩም በገና እንደሚይዙ በታላቅ ድምጽም እንደሆነ ይገለጣል። በሌላ በኩል ደግሞ በአውሬውና በምስሉም በስሙም ቁጥር ላይ ድል የነሱት የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ በኅብረት ሲዘምሩ በራዕይ እንዳየ ከነመዝሙሩ ዮሐንስ ጽፎልናል። (ራእይ 15፤2-4)

በማንኛውም መንፈሳዊ ጉባዔ ላይ የማኅበር መዝሙር ዛሬም ቢሆን ትልቅ ቦታ ሊኖረው ይገባል። በመዘምራን እየተዘመረ ማኅበሩ በመንፈስ ሊያዳምጥ ይችላል። የመዝሙር ጸጋ ያለውም አንድ ሰው አዲስ ቅኔ እየተዘመረ ማኅበሩ ሊሰማው ይችላል። ከዚህ ሁሉ የሚበልጠው ግን ማኅበሩ በአጠቃላይ በአንድ መንፈስ በታላቅ ድምጽ በተሰበረ ልብ መዘመር ሲችል ነው። እኛ ክርስቲያኖች ከኪሩቤልና ከሱራፌል ጋር እንዲሁም ከእእላፍ አእላፋት መላእክት ጋር ኅብረት አለን። ስለሆነም ከእነርሱ ጋር አንድ ድምጽ ሆነን ስለታረደው በግ ልንዘምር ይገባናል። ያለዚያ ግን ይመጣል የተባለው የዓመፅ ሰው የአውሬው መንፈስ ድል ሊነሳን ይችላል። ይህ እንዳይሆን ግን ከአሁኑ የአውሬውን ፍላጐትና መንፈስ ድል ነስተን እንደ እነዚያ ቅዱሳን አምላካችን በዝማሬ ልናመሰገን ልንኖር ይገባናል።

## መዝሙር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በጥንታዊ ቋንቋችን በግእዝ በተዘጋጀው መዝሙር እጅግ የበለጸገች እንደሆነ ለዓለም የታወቀ ታሪክ ነው። የዚህ መዝሙር ጀማሪ የሆነው ቅዱስ ያሬድ የተባለው የቤተ ክርስቲያናችን አባት ነው። ከዚህ አስቀድመን ግን ከቅዱስ ያሬድ በፊት መዝሙር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እነደነበር እንመለከታለን።

ከቅዱስ ያሬድ በፊት መዝሙር በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ያሬድ በፊት ስለነበረው የመዝሙር ሁኔታ እስከአሁን እርግጠኛ ታሪክ አልተገኘም። ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ከሌዋውያን ጋር ወደ አገራችን የገባ እንደመሆኑ መጠን ልክ በእስራኤል በዳዊት ሥርዓት ይዘመር እንደነበር በአገራችንም ይዘመር ነበር ተብሎ ሲገመት ወደ እውነት የቀረበ ይሆናል። ከዚህም ሌላ መዝሙረ ዳዊትን ቀስ ብሎ በንባባዊ ዜማ ይዘመር ነበር እንጂ በዚያን ጊዜ ድምጽን ከፍ አድርጐ መዘመር እንዳልነበረ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ታሪክ ይናገራል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን የተሻገረች እንደመሆኗ መጠን በሌዋውያን ሥርዓት የአዲስ ኪዳን መዝሙር ልንዘምር እንችላለን። በተለይም የዮሐንስ ራዕይ ላይ የተገለጠው የዚህ ዓይነት አዘማመር ነው። ንባባዊ ዜማም እንደተዘመሩ ያህል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል። ዛሬ ግን ድምጻቸው ተለይቶ እንዲሰማ በመጮኽ እያዜሙ ካልዘመሩ በቀር በዜማና በድምጻቸው የሚመኩ ስሜታውያን ጥቂቶች አይደሉም። ነገር ግን በተለይም በድምጻቸው የማይታዘዝላቸውና የልሳን (የአንደበት) ችግር ያለባቸው ሰዎች በቀስታ በንባባዊ ቢያመሰግኑት በዜማ ከቀረበው መዝሙር እኩል ይቀበልላቸዋል። እግዚአብሔር የሚያየው ዋናው ነገር በተሰበረ ልብ የቀረበለትን የመዝሙሩን መልዕክት እንጂ ዜማውን አይደለም።

## ቅዱስ ያሬድ

ያሬድ ማለት በእብራውያን ቋንቋ «መውረድ» ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን የሄኖክ አባት በዚህ ስም ተጠርቶ ነበር። (ዘፍ 5፤18) ታላቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድ ይኖር የነበረው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአጼ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት ነበር። የተወለደውም በትግራይ ክፍለ ሃገር በአክሱም ከተማ ሲሆን ዘመኑም በ505 ዓ.ም. ሚያዚያ 5 ቀን ነው። አባቱ ይስሐቅ የሚባል ሲሆን እናቱ ደግሞ ክርስትና ትባል ነበር።

ቅዱስ ያሬድ የተማረው የአክሱም ገበዝ ከነበረው የእናቱ ወንድም ከሆነው ከአጐቱ ከጌዲዮን ዘንድ ነበር። ከመዝሙረ ዳዊት ጀምሮ መኃልየ ነብያት፣ መኃልየ ሰሎሞንን፣ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ብሉይ ኪዳንንና የሌሎችንም መጻሕፍት ቁጥራቸውንም አውቆ በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በዲቁና ሲያገለግል ይኖር ነበር። ከሃያ አምስት ዓመት እድሜው በኋላ በመምህሩ እግር ተተክቶ የመጽሐፍ መምህር ሆኖ ስለነበር ቅዱስ ያሬድ በአባ ሰላማ ከሴቴ ብርሃን ጊዜ ሊቀ ካህናት ከነበረው ከእንበረም ወዲህ አራተኛ የመጽሐፍ መምህር ሆኖ ተቆጥሯል።

ቅዱስ ያሬድ ይህን ያህል በቅዱሳት መጻህፍት ሊቅ ስለነበር ያዘጋጃቸው የዜማ ድርሰቶች ከቅዱሳት መጽሐፍት ጋር የሚስማሙና የተውጣጡ ናቸው። ድርሰቱንም ያዘጋጀው በሥርዓት ሲሆን በአራቱ ክፍል ዘመናት እንዲነገር አድርጎ ነበር። ንጉሡ አጼ ገብረ መስቀል በቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰት ተደንቀውና ተመስጠው የቅዱስ ያሬድን እግር ወጉት። ድርሰቱንም እንዲቀበሉ ለካህናቱ ሲነግሯቸው በዚያን ጊዜ የነበሩት ካህናት በምቀኝነት አንቀበልም ብለው እንደነበርና ምህላ ተይዞ ጌታ በራእይ በዕለተ ዓርብ እንደተሰቀለ ሆኖ ለሕዝቡ በመታየቱ ምክንያት እንደ ተቀበሉት በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ይነገራል። ቅዱስ ያሬድ ድርሰቱን ያዘጋጀው ከ540-560 ዓ. ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

ይህ የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ሳዊራ፣ መንክር፣ እስክንድራ፣ በድር የተባሉ አራት ደቀ መዛሙርት ነበሩት። እነዚህን ደቀ መዝሙርቱን እስከትሎ እንደ ጣና ኃይንት የመሳሰሉትን የተለያዩ የአገራችንን ክፍሎች እየጐበኘ ዜማውን እንዳስተማረ ታሪኩ ያስረዳል። ስለ ውጪውም ዓለም ቢሆን ቅዱስ ያሬድ እንግዳ አይደለም። ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ የሆኑትን አባ ጽንጣሌዎንን ስለ ውጪው አገር ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ባሕል እየጠየቀ ከማወቁም በላይ ከአንዴም ሁለቴ ወደ ውጪ ሃገር ሄዶ በመጐብኘት ዓለም አቀፋዊ መረዳት የነበረው አባት እንደነበር ከታሪክ እንረዳለን። ቅዱስ ያሬድ ምድራዊ ሕይወቱን ፈጽሞ ያረፈው ግንቦት 11 ቀን 571 ዓ. ም. ነው። (ተሰወረ የሚል ታሪክም በቤተ ክርስቲያናችን አለ።)

የቅዱስ ያሬድ ትምህርት ለዚህ ዘመን ትውልድ ሊደርስ የቻለው ቅዱስ ያሬድ ለደቀ መዛሙርቱ በማስተማሩ ነው። ደቀ መዛሙርቱ እየተማሩና እየጻፉ ለተከታዮቻቸው በማስተማር አስተላልፈውልናል። ሆኖም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዮዲት እና በግራኝ ጊዜ ስትሰደድ ሊጠፉ እየተቃረበ እንደገናም በእግዚአብሔር ፈቃድ ትንሣኤ በማግኘት እስከ ዘመናችን ሊደርስ ችሏል።

እኛም መንፈሳዊ ልጆቹ ታሪክን በመተረክ ብቻ ሳንወሰን መዝሙሩንና አዘማመሩን በማወቅ እግዚአብሔርን ልናመሰግንበት ይገባል። በተለይም በአሁኑ ጊዜ ይህ መዝሙር ከነዜማው በአማርኛ

ቋንቋ ተዘጋጅቶ ከሕዝቡ ቢደርሰው ወይም ሁሉም ግዕዝን የሚያውቅበት ዘዴ ቢፈጠር ታሪኩ ከመጠበቁ ጋር ሕዝቡ ትርጉምን እያወቀ ከካህናቱ ጋር አብሮ መዘመር ይቻል ነበር። ምእመናን ከዳር ሆነው በተመስጦ እየተመለከቱ መዘመር እየፈለጉ ስለማያውቁ ይቸገራሉ። ዛሬ በየሰንበት ትምህርት ቤቱም ቢሆን በአማርኛ ቋንቋ በአብዛኛው የሚዘመሩ መዝሙሮች በአንዳንድ ወንድሞችና እህቶች ጥረት የተደረሱ አዳዲስ መዝሙሮች ናቸው። ይህ የሚደገፍ እንጂ የሚነቀፍ ባይሆንም የቅዱስ ያሬድን መዝሙር ከነዜማው ለምእመናን በሚገባቸው የአማርኛ ቋንቋ አዘጋጅቶ የሚያቀርብለት ዳግማዊ ያሬድ ለቤተ ክርስቲያን ዛሬም ያስፈልጋል።

## አምስቱ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶች

ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው የሁሉ የሆኑት አምስት የድርሰት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) ድጓ ለ) ጾመ ድጓ ሐ) ዝማሬ መ) መሥዋዕት ሠ) ምዕራፍ

ከእነዚህ ሌላ አንቀጸ ብርሃን የሚባል ድርሰት የቅዱስ ያሬድ ድርሰት እንደሆነ ታሪክ ያስረዳናል። ቅዱስ ያሬድ የራሱን ድርሰት ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ድርሰቶች ለምሳሌ ውዳሴ ማርያምን አሥራ አራቱን ቅዳሴ ዜማ እንዳወጣላቸው በትውፊት ይተረካል። ከዚህ ቀጥለን አምስቱን የቅዱስ ያሬድን ድርሰቶች በየተራ እንመለከታለን።

### *1ኛ) ድጓ*

ድጓ ማለት ልቅሶ/ሙሾ ማለት ነው። ይኸውም መዝሙር ሐዘን ነው። ድጓ በአራት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም፥

1) ዮሐንስ ምድቡ ከመስከረም 1 እስከ ኅዳር 30 ቀን
2) አስተምህሮ ምድቡ ከታኅሣሥ 1 እስከ መጋቢት 30 ቀን
3) ጾመ ድጓ ምድቡ በወርኃ ዓቢይ ጾም
4) ፋሲካ ምድቡ ከሚያዚያ ወይም ከትንሣኤ እስከ ጳጉሜን መጨረሻ

### *2ኛ) ጾመ ድጓ*

ይህ ክፍል እዚህ ላይ ራሱን ችሎ ቢቀርብም ሦስተኛው የድጓ ክፍል ነው። ቃሉ እንደሚያመለክተው ይህ ክፍል የሚዘመረው በወርኃ ጾም ነው። መዝሙሩንም በነገህ፣ በሠለስት፣ በቀትር፣ በሠርክ እንዲሁም በሌሊት እንዲዘመር ሆኖ የተዘጋጀ ነው። በውስጡም ያለው ፍሬ ሃሳብ የጾምና የጸሎትን ጠቃሚነት የሚያስተምርና ታላቅ ምስጢር ያለው ነው። የተማሪዎችም የመጀመሪያው የትምህርት ደረጃቸው ጾመ ድጓ ነው።

### *3ኛ) ዝማሬ*

ዝማሬ ማለት እንደ መዝሙር ሁሉ ምስጋና ማለት ነው። ዝማሬ የማኅበር ምስጋና ሲሆን የሚዘመረውም በቅዳሴ ጊዜ ከድርገት በኋላ ነው። ይኸውም ጌታችን ሐዋርያት በምሴተ ሐሙስ ከሥጋ ወደሙ በኋላ መዘመራቸውን መሰረት በማድረግ የሚዘመር ምስጋና ነው። ቅዳሴው ዕዝል ከሆነ ዝማሬውም በዕዝል ዜማ በመቋሚያ ብቻ ይዘመራል። ቅዳሴው ግዕዝ ከሆነ ግን ያለ መቋሚያ በአንድ ወይም በሁለት መዘምራን እየተቃኘ በብዙዎች መዘምራን ድምጽ እየታጀበ በግዕዝ ዜማ ይዘመራል። ዝማሬ በሦስት ይከፈላል። እነርሱም፥

1) ዝማሬ 2) አኰቴት 3) ምስጢር ናቸው።

### *4ኛ) መሥዋዕት*

መሥዋዕት ማለት ምልልስ ማለት ነው። በግራና በቀኝ እየተመላለሰ የሚዘመር መዝሙር ነው። በውስጡ ስለጌታ፣ ስለእመቤታችን፣ ስለጻድቃንና ስለሰማእታት፣ ስለደናግልና መነኮሳት፣ እና ስለቅዱሳን መላእክት ከመናገሩም በላይ ስለሙታን ፀአተ ነፍስና እረፍተ ነፍስ በስፋት ያዟል። ስለዚህ ይህ መዝሙር በአብዛኛው የሚዘመረው ለሙታን በሚደረገው በጸሎት ፍትሐት ላይ ነው።

ሆኖም በጌታና በእመቤታችን፤ በመላእክትና በጻድቃን ሰማእታት በዓል ላይም በአገልግሎት ይውላል። መሥዋዕት ከዝማሬ ጋር የሚሰጥ ትምህርት ሲሆን ምንም ዓይነት የውስጥ አከፋፈል የለውም።

### 5ኛ) ምዕራፍ

ምዕራፍ ማለት ማረፊያ ማለት ነው። የዜማውን ማሳረፊያ የሚነግረን ስያሜ ነው። የምዕራፍ ትምህርት አሰጣጥ እንደ ሌሎች የያሬድ ድርሰቶች መጽሐፍ ዘርግቶ ሳይሆን በውስጡ ያሉትን ትምህርቶች በቃል በማጥናት የሚሰጥ ነው። የምዕራፍ ድርሰት መስተጋቦዕ፣ አርባዕት፣ አርያም፣ ሠልስት፣ መወድስ፣ ስብሐት ነግህ እያለ የሚሄድ የውስጥ አከፋፈል አለው። በአጠቃላይ ግን ምዕራፍ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም፥

1. የዘወትር ምዕራፍ፥ በዓመት ውስጥ ባሉ ሳምንታትና በዓላት ወቅቱን ጠብቆ የሚዘመር፤
2. የጾም ምዕራፍ፥ በዐብይ ጾም እና በአንዳንድ የምህላ ቀኖች የሚባል ነው፤

ማስገንዘቢያ፥ ቅዱስ ያሬድ በሕይወት ዘመኑ ትምህርትና ጸሎት ምስጋናም የሆኑትን እነዚህን የመዝሙር ድርሰቶች በጽሑፍ ትቶልን አልፏል። ዛሬ ግን እንኳን አዲስ ድርሰት በቤተ ክርስቲያን ልናበረክት ቀርቶ ያለውንም አጥንቶ ለመዘመር ብዙዎቻችን አልቻልንም። ስለዚህ የግዕዙን ቋንቋ አውቀን እነዚህን የያሬድ ድርሰቶች አጥንተን ለመዝሙራችን ድርሰቶች ምንጭ በማድረግ እየተረጎምን ለሕዝቡ የሚሆን የአማርኛ መዝሙሮችን ማዘጋጀት ይገባናል።

## ማኅሌት (አቋቋም)

ማኅሌት የሚለው ቃል ኀለየ ከሚለው ግሥ የተገኘ ቃል ነው። ኀለየ ማለት ዘፈነ ማለት ስለሆነ ማኅሌት ማለት ደግሞ ዘፈን ማለት ነው። ሆኖም ይህ ቃል መንፈስዊ ምስጋናን እንጂ ዓለማዊ ዘፈንን አያመለክትም። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ማኅሌት በመቋሚያ፣ በከበሮና በጸናጽል በዓቢይና በንዑስ መረግድ፣ በወረብ የሚዘመረውን መዝሙር ያሳያል። አቋቋም የሚባለው ግን ትምህርት ነው።

### ታሪካዊ አመጣጡ በአጭሩ

ማኅሌት እንደአሁኑ ይዞታ ሳይሆን ወደቁሙ ዜማ በማስጠጋት ከቅዱስ ያሬድ ጀምሮ የነበረ ነው። ነገር ግን ደርሰው የሚባለው በጎንደር ዘመነ መንግሥት የነበረው ባሕታዊ ኤስድሮስ የሚባለው ሊቅ ነው። ላህይና ቃናው እየተሻሻለ ሊመጣ የቻለው ደግሞ በአፄ አድያም ሰገድ (1665 እስከ 1689 ዓ. ም.) ዘመን ነው። ለዝማሜና ለመረግድ፣ ለከበሮና ለጸናጽል እንዲያመች ሆኖ የአቋቋም ባሕልና ሥርዓት ከበፊቱ በበለጠ የተሻሻለው በአፄ በካፋ ዘመን በነመሪጌታ መብረቄ፣ በመሪጌታ ነገድጓድ፣ በእነ ጸሐፊ ትዕዛዝ ድሜጥሮስ በተባሉት ሊቃውንት አማካይነት ነው። ወንበር ዘርግቶ ማስተማር የጀመረው ግን በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት 1882 ዓ. ም. የድርቦሾች ጥፋት በኋላ የአማረ እሸቱ ተማሪ በነበሩት በመሪጌታ ላቀው ፈለቀ አማካይነት ነው። ሆኖም መሪጌታ ላቀው ፈለቀ ከትምህርት ጓደኛቸው ከመሪጌታ ገብረ ዮሐንስ ጋር ወዝ በመለዋወጥና ይትብሐል በማሻሻል ተለያይተዋል።

ከዚህ ጀምሮ በየጊዜው በሚነሱት መምህራን አማካይነት ወዙና ልህዩ እየተለያዩ መጥቶ የላይ ቤት፣ የታች ቤት፣ ሳንኳ፣ ጎንደሬ፣ ተክሌ የሚባለው ልዩነት ሊፈጠር ቻለ። ሆኖም ልዩነቱ የአዘማመሩና የአቀራረቡ ሁኔታ ስለሆነ ብዙ የጐላ ልዩነት ነው ለማለት አይቻልም። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ሁሉንም አስተባብሮ የያዘ የእርቅ ቤት የሚባል አቋቋም አለ።

## ሥርዓተ ማኅሌት

በዚህ ክፍል የማኅሌት ቅደም ተከተሉን አፈጻጸሙን እንመለከታለን። እያንዳንዱንም ሥርዓት ምስጢራዊ ትርጉም ያለው በተለይም የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ የሚያሳይ ሥርዓት እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይናገራሉ።

ቅደም ተከተሉ፥

1- ካህኑ አስርቆት አድርጐ በጸሎት ይጀምራል።
2- ሚካኤል ሊቀ መላእክት ስዕል በእንቲአነ የሚለውን እየተቀባበሉ ይባላል።
3- ካህኑ አቡነ ዘበሰማያት ይላል።
4- «ስምዐኒ እግዚኦ ጸሎትየ» በመሪና በተመሪ በአንሺ ይባላል።
5- «ሰብሕ ወውዱስ ዘሣረረ ኵሎ ዓለም በአሐቲ ቃል» የሚለው ምስጋና ይባላል።
6- ሰላምታ ይባላል በዚህ ውስጥ ከመልክአ ሥላሴ ገብቶ የሚባል አለ።
7- «ዘመንክር ጣዕሙ» ከተባለ በኋላ ከበዓሉ ነግሥ ይባላል።
8- ከዚህ በኋላ እንደየ በዓሉ መልክአ መልክእ ይባላል።
9- ከሚመረጉዱት መልኮች ቀጥሎ ዚቅ ይገባል ወረብ ይወረባል።
10- መልክአ ካለቀ በኋላ ካህኑ አቡነ ዘበሰማያት ይላል።
11- ከዚያም ተመሲሊኪ ይባልና እንደገና አቡነ ዘበሰማያት ይሰጣል።
12- ስንክሳር ይነበባል።
13- አርኬ ይደረሳል።
14- ምልክአ ውዳሴ ይባላል።
15- ምስባክ ይባላል።
16- ምልጣን እስመ ለዓለም ይባላል።
17- በመጨረሻም ኪዳን ይደርሳል።
18- ጸሎተ ኑዛዜው ተሰጥቶ ቅዳሴው ይቀጥላል።

ይህ ሁሉ ሥርዓት የሚፈጸመው፥

1) በቁም ዜማ 2) በዓቢይና በንዑስ መረግድ 3) በአጽሕሶ (በሽብሽባ)
4) በጽፍዐት 5) በመሪና በተመሪ በአንሺ ነው።

ሁሉንም ግን ከልብ በተሰበረ መንፈስ ልንዘምር ይገባል።

## የመዝሙር ግጥምና ዜማ

አንድን መዝሙር ልብ የሚመስጥ የሚያደርገው የግጥምና የዜማ ጥራት ነው። ምንም እንኳን እግዚአብሔር የአንድን መዝሙር የሥነ ግጥም የዜማ ሁኔታ ባይመለከትም ክርስቲያኖች ሁሉም ነገር የተሟላለት (የተዋጣለት) መዝሙር ለእግዚአብሔር ማቅረብ ይገባቸዋል። በእርግጥ ያለግጥም በስድ ንባብም ማዜም ይቻላል። አብዛኛውን ጊዜ ግን መዝሙር በግጥም የሚዜም ሆኖ እናገኘዋለን። ስለዚህ መዝሙሮችን ለማዘጋጀትም ሆነ የተዘጋጀውንም በተረዳ አእምሮ፣ በተሰበረ ልብ ለመዘመር የግጥምንና የዜማውን ጸባይ ማወቅ ያስፈልጋል።

### ሀ. የመዝሙር ግጥም

ግጥም ማለት በፊደል ወይም በቃል ወይም በምስጢር የገጠመ የስንኞች ድርደራ ነው። ከመዝሙር ዳዊት ሌላ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጽሐፈ ኢዮብ (ከምዕራፍ 3 እስከ 41) መጽሐፍ ምሳሌ የመሳሰሉት መጻሕፍት በእብራይስጡ ቋንቋ በግጥም የተጻፈ ከመሆናቸውም በላይ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተመዘገቡት መዝሙሮችም በግጥም የተዘመሩ ናቸው። (1ኛ ሳሙ 2፤1-10 ። 1ኛ ዜና 16፤8-36 ። ሉቃ 1፤46-55 ። ሉቃ 1፤68-79) ... ወዘተ።

በግጥም ውስጥ ያሉት ሁለት ክፍሎች በሐሳብ ወይም በአቀራረብ በሦስት መንገድ ይታያሉ። ይኸውም፥

1. ሁለተኛውም ለመጀመሪያው አስረጅ በመሆን የመጀመሪያውን ሐሳብ እየተደገፈ የሚገጠም ነው።

ለምሳሌ፣ ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር ናት
ዓለምም በእርስዋ የሚኖሩ ሁሉ።
እርሱ በባሕሮች ላይ መሰርቷልና
በፈሳሾችም ላይ አጽንቷልና። (መዝ 23፤1-2) ይላል።

ይኸውም ባሕርን በመመስረቱና በፈሳሾች ላይ በማጽናቱ ምክንያት ምድርና መላዋ ዓለምም በእርስዋ የሚኖሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ናት ማለት ነው።

2. የሁለተኛው ሐሳብ ለአንደኛው የግጥም ክፍል ሃሳብ ተቃራኒ ሆኖ የሚቀርብም የግጥም ኣይነት አለ። ለምሳሌ፣ ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉ
እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን እነርሱ ምድርን ይወርሳሉ።
(መዝ 36፤9) ይላል።

በዚህ ግጥም እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ምድርን የመውረሳቸው ሐሳብ ክፉ አድራጊዎች ለመጥፋታቸው ሐሳብ «ግን» በሚለው አፍራሽ ቃል ተቃራኒ ሆኖ ቀርቧል። በዚህም የእግዚአብሔርን ፍርድ አድንቆ ዘምሯል።

3. ከሁለቱም የግጥም ክፍሎች ያሉ ባለቤቶችንና ተሳቢዎች ግሦችን ሌሎችም የሚገናኙበትና ምስጢሩን የሚያብራራበት ግጥም አለ።
ለምሳሌ፣ የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው ልብን ደስ ያሰኛል
የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩክ ነው ዓይንንም ያበራል።
(መዝ 18፤8) ይላል።

«የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው» የሚለው «ልብን ደስ ያሰኛል» ከሚለው ጋር የእግዚአብሔር ትእዛዝ «ብሩክ» ነው የሚለው ዓይንንም ያበራል ከሚለው ጋር በሥነ ጽሑፍና በምስጢር የተስማማና የተገናኘ አባባል ሆኗል። ከዚህም ሌላ ግጥም ሊስተዋል እንዲችልና ሲዘምሩትም እንዳያስቸግር ዜማ መስበር የለበትም።

የአንድ መዝሙር ግጥም ልክ እንደሰቡበት መልእክቱን የተከተለ ርእሱን የጠለቀ ሊሆን ይገባዋል። በቅኔ መንገድ ቢቀርብ በበለጠ ጥሩ ይሆናል። በአዝማች ወይም ያለ አዝማች በቁሙ እንዲባል ሆኖ ሊዘጋጅ ይችላል። በቤተ ክርስቲያናችን የነግስና የመልክእ አቀራረብ በግጥም የተዘጋጀ ነው። መዝሙር ምስጋና ብቻ ሳይሆን ትምህርትም በመሆኑ ግጥሙ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚስማማ ለትምህርትን ለተግሣጽ የሚሆን ስለ እግዚአብሔር ገናናነት ስለተደረገልን ነገር የሚመሰክር በተለይም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራ የምንመሰክርበት ሊሆን ያስፈልጋል።

## መዝሙር እንዴት መዘመር አለበት?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው ይላል። (1ኛ ቆሮ 14፤26) ደግሞም በመዝሙርና በመንፈሳዊ ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ ይላል። (ቆላ 3፤16 ። ኤፌ 5፤19) እንዲህ ከሆነ ክርስቲያኖች ለአምልኮትም ሆነ ለወንጌል ስብከት በቤተ ክርስቲያን ሲሰበሰቡ እንዲሁም በማኅበር እና በግል መዘመር አለባቸው። ነገር ግን ክርስቲያኖች ሲሰበሰቡ ለእያንዳንዱም መዘመር ለእያንዳንዱም ትምህርት አለውና መዝሙር የጸጋ ስጦታቸው የሆነ ተሰባስበው መዘምራን በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ። ቅዱስ ዳዊት በመገናኛው ድንኳን እንዲያገለግሉ ያደራጃቸው መዘምራን ነበሩ (2ኛ ዜና 29፤25-28) ወንዶችም ሴቶችም መዘምራን መሆን ይችላሉ። የጾታ ልዩነት የለም። ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ከተመለሱት እስራኤላውያን ሁለት መቶ ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩ። (ዕዝራ 2፤65-66) በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን የካህናት መዘምራን አሏት። እንዲሁም በየሰንበት ትምህርት ቤቱ ቋሚ የወንዶችና የሴቶች መዘምራን አሏት።

**በመዘምራን ስለሚያገለግሉ**
በአጭሩ ስለመዘምራንና ስለመዝሙር ይህን ያህል ካየን አሁን ደግሞ «መዝሙር የሚዘምሩት ሰዎች እንዴትና ምን መሆን አለባቸው?» የሚለውን የመዘምራንን ነገር እንመልከት።

መዘምራን ከመዘመራቸው በፊት የመዝሙርን ምንነት ማወቅ ዜማን ብቻ ሳይሆን ቃሉን ማስተዋል ለምን/ለማን እንደሚዘምሩ ማወቅ ዘምረው ምን እንደሚያገኙ መረዳት አለባቸው።

የመዝሙርን ምንነት ያላወቀ ዘማሪ መዝሙር ጊዜ ማሳለፊያ ወይም መዝናኛ ሆኖ (መስሎ) ሊታየው ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሰው በመዘምራን መካከል ካለ መዘምራን ተገንዝበው የሚዘምሩት መዝሙር ሌሎች እንዳይድኑበት እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ይሆንግል። መዝሙርን መጀመሪያ ያስተማረው እግዚአብሔር ነው ሰው አይደለም። ማናኛውም ዘማሪ በሚዘምርበት ጊዜ ያንን መዝሙር እግዚአብሔር በአፉ ውስጥ እንዳስቀመጠለት መገንዘብ አለበት።

ዘማሪው እንደዘፈን የሚቆጥረውና ያልተረዳው ከሆነ የሚዘምረው መዝሙር ሰዎችን በፍቅረ እግዚአብሔር የሚያጠምድ አይሆንም። የሚዘምረውን መዝሙር የማያውቅ ከሆነ እየዘመረ እንኳ ዓይኑ ይቅበዘበዛል። ሰውን ብቻ ይመለከታል። ዘሩ (ቃሉ) እና ዜማው ይደናገረዋል። ስለዚህ አገልግሎት ሰዎችን በማቅረብ ፈንታ ሰዎችን የሚገፋ ይሆናል። ዘማሪው ከዚህ ሁሉ እንዲድንና እንዲጠበቅ መዝሙሩን በሚገባ ማወቅ አለበት። ይህም ማለት ዜማንና ዘሩን ብቻ ሳይሆን በማን ፊት እንደሚዘምር ማወቅ አለበት።

መዘምራን የምእመናንን ልብ ለእግዚአብሔር ቃል የለሰለሰ መሬት ለማድረግ በዝማሬ ማረሻ የሚያርሱ እና የሚቀሰቀሱ የሚያለሰልሱ መሆን አለባቸው። በሚያሳዝነው መዝሙር ላይ የደስታፊት ገጽታ፤ በሚያስደስተው መዝሙር ላይ የሐዘን የትካዜ ገጽታ ሊታይባቸው አያስፈልግም። የሰውነታቸው ሁኔታ (እንቅስቃሴ) በመዝሙሩ ጋር የሚሄድ መሆን አለበት። በተለይ ግን መዘምራን የመድረክ ላይ ክርስቲያን ብቻ እንዳይሆኑ መጠንቀቅ አለባቸው። በአሁኑ ሰዓት ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ችግር የሰባኪያን እንደስብከታቸው፤ የመዘምራን እንደመዝሙራቸው አለመሆን ነው። «ጹሙ ወጸልዩ ለእግዚአብሔር ተቀነዩ» ጹሙና ጸልዩ ለእግዚአብሔርም ተገዙ ብሎ ጠዋት የዘመረው ለሰዓት በኋላ ደግሞ ሲጾም ሲጸልይ ለእግዚአብሔር ሲገዛ አይታይም። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ዘማሪው የሚዘምረው ዜማውን ብቻ እንጂ ቃሉን ጭምር ስላልሆነ ነው። እግዚአብሔር ከዜማ በፊት የሚያየው የሚያዜመውን ሰው ሕይወት ነው። በዝማሬ የሚታለል (የሚሸነገል) አምላክ አይደለም። የመዘምራኑ የውስጥ ሕይወት ከመዘመራቸው በፊት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የለዘበ፣ የጣፈጠ እና ልዑል እግዚአብሔር ሕዝብን የሚባርክበትና የሚለውጥበት ልቦና ሊኖራቸው ይገባል። መዘምራን የድምፅ የአለባበስ፣ የአቋቋም የአፍ አከፋፈት ተወዳዳሪዎች መሆን የለባቸውም። ሱራፌልና ኪሩቤል የሚያመሰግኑትን ጌታ ለማመስገን ከእርሱም ጋር ለመነጋገር የተቀደሰ አንደበትና የተተኮሰ ከንፈር ነው የሚያስፈልገው። (ኢሳ 6፤5-7)

መዝሙር የሚዘምረው ለእግዚአብሔር በእርሱ ፊትና በእርሱ ቤት የሚዘመር ምስጋና ነው። በቤቱ የሚዘመር የተቀደሰ ሕይወት ነው። መዘምራን በሚዘምሩበት ጊዜ ከፊታቸው ሰማያዊ ንጉስ ኢየሱስ ክርስቶስ አለና በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ እንዲቆሙ ጊዜ ወስደው መጸለይ አለባቸው። ያለዚያ ግን በዚያ በእግዚአብሔር መድረክ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስን ጋርደው እነርሱ ለመታየት የተዘረጉ መጋረጃዎች ይሆናሉ ማለት ነው። የእግዚአብሔር አገልጋይ ደግሞ ዓላማው የእግዚአብሔር ነጸብራቅ መሆን ስለሆነ እንደመስታወስ የእግዚአብሔርን ብርሃን የሚያንፀባርቅ ሕይወት ሊኖራቸው ይገባል።

አቤት መዘመራቸው (አቤት አሰላለፋቸው) ለመባል ብቻ መድረክ ላይ የሚወጡ መነናጸፊያቸው ክርስቶስ ኢየሱስ ያልሆነ መዘምራን ለማኅበራቸውም ሳይቀር የውድቀት ምክንያት ይሆናል። ስለዚህ በአገልግሎታቸው ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ጎልቶ እንዲታይ በመዝሙራቸው ያዘኑ እንዲጽናኑ፤

የተሰበሩ እንዲጠገኑ፤ የተጠራጠሩ እንዲያምኑ ዘወትር በፍቅርና በሰላም በመንፈስ በኅብረት በመጸለይ የተጉ፣ የማይተማሙ፣ የማይኮራረፉ መሆን አለባቸው። እንዲህ ከሆነ የሚዘምሩት መዝሙር የእስር ቤት መሰረት የሚያናውጥ ሰንሰለት የሚበጥስ ነፍሳትን የሚያድን ይሆናል። (የሐዋ ሥራ 16፤16-34)

በዚህ ዓለም ያሉ ሰዎች በመሪዎችና በነገሥታት ፊት ዘፍነውና ቦርቀው የሚሰጡአቸው ጊዜያዊና ኃላፊ የሆነ የኃጢአት ውጤት ነው። (ማቴ 14፤1-12) ለእግዚአብሔር መዘመር ግን በምድር ሰላም እና የሕሊናን ዕረፍት በመጨረሻም የዘለዓለምን ሕይወት ያቀዳጃል ያወርሳል። («አገልግሎት» በዲያቆን እንግዳ ቸሩ ገጽ 4-5)።

መዘምራን ልክ እንደ ወንጌል ሰባኪዎች እንደሌሎችም አገልጋዮች በክርስቲያኑ ሕዝብ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣልና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የታነጸና ለሌላው ብርሃን መሆን የሚችሉ እንዲሆኑ በጾምና በጸሎት ሊተጉ ይገባል።

## ማጠቃለያ፥

ዘምሩ ለአምላክችን ዘምሩ
ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ
እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና፣
በማስተዋል ዘምሩ።
መዝ 45፤5-6

እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ አምላክና ንጉሥ ነው። ስለዚህ ምስጋናውም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ነው። እግዚአብሔር በባሕርይው የተመሰገነ ነው። ስለዚህ ብናመሰግነው የምንጠቀመው እኛ መሆናችንን ልናስተውል ይገባናል። እስከ አሁን ድረስ ስለመዝሙር ያለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ትውፊታዊ ትምህርት አይተናል። ነገር ግን ይህ ትምህርት ስለመዝሙር በጥልቅ እንድናውቅ ሳይሆን በማስተዋል እንድንዘምር ለማድረግ የተሰጠ ትምህርት ነው።

መዝሙር በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ሃይማኖታዊ ፍቅር የሚገለጽበት መንገድ ነው። በእኛ ላይ ያለው ዓለማዊ ፍቅር ነው። (መኃልየ 2፤4) በላይ ቤትና በታች ቤት ዜማ በሌሎችም የዜማ ልዩነቶች እየተጣላንና እየተነቃቀፍን ጥውም የሆነውን ማኅሌት ፍቅር አልባ ልናደርገው አይገባም። በየሰንበቱ ትምህርት ቤቱም በሚፈጠሩ የዜማ ልዩነቶች ምክንያት ፍቅርን በማደፍረስ እግዚአብሔርን እናመስግን ብንል የከንፈር ምስጋና ይሆናል። መዝሙሮች ሁሉ አንድ ወጥና ተመሳሳይ ያሬዳዊ ዜማ እንዲኖራቸው የሚመለከታቸው ሁሉ ጥረት ሊያደርግ ይገባል። ከዚህም ሌላ እውነትንና እውነተኞችን እየተጸየፉና እየጠሉ ድኃ እየበደሉ ጻድቃን እያጨነቁ ፍርድ እያጣመሙ እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚወድ ፍቅሩን በማስተዋል የሚዘመረው መዝሙር በእግዚአብሔር ተቀባይነት የለውም። (አሞጽ 5፤23) ስለዚህ በዚህ ሁሉ ለሰማያዊው ንጉሥ ለእግዚአብሔር በፍቅር መዘመራችንን ልናስተውል ይገባል።

አንዳንድ ጊዜ መዝሙር ሲዘመር ከመጠን በላይ ጩኸት ሲበዛ በሰሜት በመነዳት ከሥርዓት ውጪ መሆን ይታያል። ይህ ማንን እንደምናመሰግን፣ እንዴት እንደምናመሰግን ምን እያልን እንደምናመሰግን ካለማስተዋል የተነሳ ነው። ስለዚህ የምንዘምረውን ምን እያልን እንደምናመሰግን አምላክ እግዚአብሔርን በኪሩቤል ጀርባ ላይ እንዲሁም በመስቀል ዙፍን ላይ ሆኖ በዓይነ ልቦና እያየነው፤ በግላችንም ሆነ ከዓለም ጋር ያደረገልንን ውለታ እያስታወስን በማስተዋል ልንዘምር ያስፈልጋል።

የስብከታችን ማዕከል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ሁሉ የመዝሙራችንም ማዕከል እርስ ሊሆን ይገባዋል። ወደ ቅዱስ ያሬድ ከተላኩት ወፎች አንዱ «አዲሱን የእግዚአብሔር

ምስጋና ሥራ እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው» ብላ እንደነገረችው መረዳት ይኖርብናል። (ያሬድና ዜማው ገጽ 23) በመጽሐፍ ቅዱስም «በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት» የሚል ቃል ይገኛል። (ቆላ 3፤17) ስለዚህ ስሙን በትሕትና እየጠራን በመስቀል ፍቅሩ እንዳዳነን እያሰብን በከንፈር ብቻ ሳይሆን በልብ በማስተዋል እንዘምርለት።

አንድ መዝሙር ታሪክ ምስጢርና መልዕክት ይኖረዋል። ይህም በመዝሙር ቃል ውስጥ ከላይ እስከታች ተያይዞ የሚገኝ ነው። ስለዚህ ዜማውን ወይም አዘማመሩን ብቻ ሳይሆን ታሪኩ ምስጢሩና መልዕክት ምን እንደሆነ እያስዋልን መዘመር አለብን። ቅዱስ ዳዊት «እዘምራለሁ ንጹሕ መንገድንም እስተውላለሁ» ብሏል። (መዝ 100፤2)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።